Washington State Office of the Attorney General

# በሕዝብ አስተዳደር ክስተቶች ውስጥ የአካላዊ ኃይል እርምጃ አጠቃቀም ምርጥ ተሞክሮዎች

ጁላይ 1፣ 2022

# በሕዝብ አስተዳደር ክስተቶች ውስጥ የአካላዊ ኃይል አጠቃቀም ምርጥ ተሞክሮዎች

በሕዝብ አስተዳደር አውዶች ውስጥ አካላዊ ኃይልን መጠቀም በመደበኛ የኃይል እርምጃ አጠቃቀም ፖሊሲ ውስጥ ላልተገለጹት ሁኔታዎች ልዩ የሆኑ አንዳንድ ስጋቶችን ያስነሳል። የሚከተሉት የሞዴል ድንጋጌዎች የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ በሕዝብ አስተዳደር ላይ በሚያወጣው ሰፋ ያሉ ፖሊሲዎች ውስጥ ለመካተት የታቀዱ ናቸው።

(1) ተልዕኮ፦ በሰላማዊ ሰልፎች እና ሕዝባዊ ረብሻዎች ወቅት የህግ ማስከበር ተልዕኮ ሀሳብን በነፃነት መግለጽን እና በነፃነት መሰብሰብን ማመቻቸት፣ ማንኛውንም አይነት ሁከት እና ብጥብጥ ማረጋጋት እና ግጭቶችን መፍታት ነው። በሰላማዊ ሰልፎች እና ህዝባዊ ረብሻዎች ወቅት አካላዊ የኃይል እርምጃን በመጠቀም ላይ የሚከተሉት ክልከላዎች እና ገደቦች መታየት አለባቸው። አለበለዚያ፣ የኃይል እርምጃ አጠቃቀም ፖሊሲ ተግባራዊ ይሆናል።

(2) ህገ-ወጥነት፦

ተሳታፊዎቹ የመናገር መብታቸውን በህጋዊ መንገድ ሲጠቀሙ፣ የህዝቡ ሁኔታ እንደ ሰላማዊ ተቃውሞ ወይም ሰልፍ ይቆጠራል። በእነዚህ አጋጣሚዎች የፖሊስ ምላሽ ላይኖር ይችላል ወይም የፖሊስ ምላሽ ካለ አካላዊ ኃይል ሳይጠቀሙ ዝግጅቱን ማመቻቸት ይሆናል።

ሰላማዊ መሰባሰቡ እንዲቀጥል በግለሰቦች ወይም በጥቃቅን ቡድኖች የሚፈጸም የተነጠለ ሕገ-ወጥተግባር በተነጣጠረ ህግ ማስከበሪያ ሊፈታ በሚችልበት ጊዜ፣ ኦፊሰሮች በህዝብ ጣልቃ ገብነት ስልቶች ጣልቃ በመግባት ሰላማዊ መሰባሰቡ እንዲቀጥል ህግ የሚጥሱ አካላትን ማስወጣት አለባቸው። በህዝብ ጣልቃ ገብነት ስልቶች በህጋዊ መሰባሰብ ውስጥ ህግ የሚጥሱ ሰዎችን በመለየት እና በማሰር ህገ መንግስታዊ መብቶችን መጠቀም እንዲቀጥል ለማድረግ የተነደፉ ተግባራት ናቸው።

በህዝብ መካከል የሚደረጉ ድርጊቶች ወይም ባህሪ በማናቸውም ሰው ላይ ጉዳት የማድረስ ወይም በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ ትልቅ አደጋ ሲፈጥሩ፣ የህግ አስከባሪ አካላት ሕገ-ወጥ መሰባሰብ እንደሆነ በማወጅ መደበኛ የመበተን ትዕዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ።

ተቃውሞውን ሕገ-ወጥ መሰባሰብ ወይም “ግርግር” ብሎ ማወጅ፣ እያንዳንዱ አካላዊ የኃይል እርምጃ አስፈላጊ እና ሕጋዊ ዓላማ ያለው መሆን አለበት የሚለውን መስፈርት አይጎዳም።

(3) አካላዊ የኃይል እርምጃ አጠቃቀም፦

በኃይል አጠቃቀም ፖሊሲ እና ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ገደቦች መሠረት በሕዝብ ውስጥ ባሉ የተወሰኑ ግለሰቦች ላይ አካላዊ የኃይል እርምጃ ለህጋዊ ዓላማ ሊወሰድ ይችላል። በሚቻልበት ጊዜ፣ ኦፊሰሮች አካላዊ ኃይልን የመጠቀምን ፍላጎት ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ በሁኔታዎች መሰረት ሁሉንም ያሉ እና ተገቢ የሆኑ የማረጋጊያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ኦፊሰሮች በሁኔታዎች መሰረት ተቃውሞን ለመቋቋም አስፈላጊ የሆነውን አነስተኛ አካላዊ ኃይል የሚጠቀሙ ሲሆን አስፈላጊነቱ ሲያበቃ የኃይል አጠቃቀምን ያቆማሉ። (RCW 10.120.020)።

በሕዝብ ውስጥ የተወሰኑ አይነት አካላዊ ኃይልን በመጠቀም ላይ ገደቦች እንደሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

(a) ችላ በማለት አለመታዘዝ

ግለሰቦች ሕገ-ወጥ ድርጊት በመፈጸም ችላ በማለት በማይታዘዙበት (ለምሳሌ፣ መቀመጥ ወይም መተኛት) ሁኔታ ውስጥ፣ አንድ የአደጋ ተቆጣጣሪ ሰላማዊ መፍትሄ ለማግኘት ከእነዚህ ግለሰቦች ጋር ለማውራት ይሞክራል። ካስፈለገ፣ ኦፊሰሮች እንዲንቀሳቀሱ ለመምራት ቴክኒኮችን ሊጠቀሙ ይችላሉ (ለምሳሌ፣ ማንሳት፣ መሸከም)። ህመም ሊያስከትሉ የሚችሉ ዘዴዎች ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

(b) ዱላ

(i) ኦፊሰሮች እንዲበተኑ ትእዛዝ ከመስጠታቸው እና እነዚህን ትዕዛዞች ለማክበር ተገቢ ጊዜ ከመፍቀዳቸው በፊት ህዝቡን ለመግፋት ዱላ አይጠቀሙም። ይህ ድንጋጌ ከአንድ የተወሰነ ሰው የሚመጣውን የጥቃት ስጋት ለመቋቋም ዱላ በሚጠቀሙ ኦፊሰሮች ላይ አይተገበርም።

(ii) ዱላ ተጠቅመው ህዝብን ወይም ግለሰቦችን ለማንቀሳቀስ የሚሞክሩ ኦፊሰሮች ከቁጥጥራቸው ውጭ በሆነ ምክንያት (ለምሳሌ የህዝብ ብዛት፣ የአካል ጉዳት፣ የአካል እንቅፋቶች፣ ወዘተ) ወደ ኋላ መንቀሳቀስ የማይችልን ማንኛውም ሰው መግፋት የለባቸውም።

(iii) ኦፊሰሮች የህዝብ መቆጣጠሪያ ዱላ ቴክኒኮችን ሲጠቀሙ የማንኛውንም ሰው ጭንቅላት፣ አንገት፣ ጉሮሮ ወይም አከርካሪ ከመምታት ለመዳን ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

(c) Projectile Impact Weapons (PIW)

(i) Projectile Impact Weapons (PIW፣ ተወንጫፊ የተጽዕኖ መሳሪያዎች) እንደ 40ሚሜ ስፖንጅ ወይም የአረፋ ኳሶች፣ PepperBall (የበርበሬ ኳስ) ወይም ተመሳሳይ ተወንጫፊ፣ የሚፈነዱ ኳሶች ወይም ቢን ባጎች ያሉ ተወንጫፊዎችን የሚያስወነጭፍ የማይገድል መሳሪያ ነው።

(ii) PIW ን በተሰበሰቡ ሰዎች ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው። ይህ ድንጋጌ ኦፊሰሮች PIW ን በሕዝብ ቁጥጥር ሁኔታዎች ውስጥ በማንኛውም ሰው ላይ ጥቃት ለማድረስ በሚያስፈራራ የተወሰነ ግለሰብ ላይ እንዳይጠቀሙ ለመከልከል የታሰበ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ኦፊሰሮች በተመልካቾች ላይ የሚደርስን አደጋ እና ሌሎች የኃይል ዘዴዎችን መጠቀም የሚቻል እንደሆነ በጥንቃቄ ማመዛዘን አለባቸው። እንዲህ ዓይነቱ አጠቃቀም የኃይል አጠቃቀም ፖሊሲን ማክበር አለበት።

(d) ሌሎች የማይገድሉ ተተኳሾች

(i) የጩኸት ፍላሽ ማዞሪያ መሳሪያዎች፣ ወይም “ፍላሽ ባንግስ” እና የእጅ ቦምብ አይነት መሳሪያዎች እንደ የመጨረሻ አማራጭ ካልሆነ በስተቀር ለህዝብ ቁጥጥር ዓላማዎች ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

(ii) ኬሚካላዊ ያልሆነ ጭስ በአደጋው ተቆጣጣሪ መመሪያ እና እሱን ለመሸከም እና ለመጠቀም ስልጣን በተሰጠው አካል ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ከእያንዳንዱ መጠቀም በኋላ፣ የአደጋው ተቆጣጣሪ ተጨማሪ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ለማወቅ ቦታውን እንደገና ይገመግማል።

(e) አስለቃሽ ጋዝ

(i) የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች በሁከት፣ በታጠረ ሰው ወይም በታገቱበት ሁኔታ ሊደርስ የሚችለውን ከባድ ጉዳት ለማቃለል አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር አስለቃሽ ጭስ ሊጠቀሙ ወይም ኦፊሰሮቹ ወይም ሌሎች ሠራተኞቻቸውን እንዲጠቀሙ ሊፈቅዱ አይችሉም። (RCW 10.116.030)።

(ii) አስለቃሽ ጭስ ከመጠቀም በፊት የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች በሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙትን እና ተገቢ የሆኑትን ለአስለቃሽ ጋዝ አጠቃቀም አማራጮች የሆኑትን ነገሮች ያሟጥጣሉ። (RCW 10.116.030)።

(iii) አስለቃሽ ጭስ መተኮስ ያለበት አስለቃሹ ጋዝ ጥቅም ላይ የሚውልበት አከባቢ ውስጥ ከፍተኛውን የስልጣን ካለው ባለስልጣን ፈቃድ ከተገኘ በኋላ ብቻ ነው። (RCW 10.116.030)።

(iv) አስለቃሽ ጭስ የመጠቀም ፍላጎት አሳውቁ።

(v) ሰዎች የኦፊሰሩ መመሪያዎችን እንዲያከብሩ በቂ ጊዜ እና ቦታ ፍቀዱ። (RCW 10.116.030)።

(vi) አስለቃሽ ጭስ ለመተኮስ በሚያስቡበት ጊዜ የአደጋው ተቆጣጣሪ በህዝቡ ላይ አጠቃቀሙ የሚያስከትለውን ጉዳት በጥንቃቄ ማመዛዘን አለበት ምክንያቱም እነዚህ መሳሪያዎች ኦፊሰሮችን ጨምሮ በአካባቢው ያሉትን ሁሉንም ሰዎች እንዲሁም በአቅራቢያው ባሉ ሰዎች ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። አስለቃሽ ጭስ ከመተኮሱ በፊት የአደጋው ተቆጣጣሪ ሠራተኞቹ እንደ ጋዝ ጭምብሎች ያሉ መከላከያ መሳሪያዎችን በትክክል መታጠቃቸውን ማረጋገጥ አለበት።

(vii) ከእያንዳንዱ መተኮስ በኋላ፣ የአደጋው ተቆጣጣሪ ተጨማሪ መተኮስ አስፈላጊ መሆኑን ለማወቅ ቦታውን እንደገና ይገመግማል።

(f) ዉሾች

የፖሊስ K-9ኦች ን ለህዝብ ቁጥጥር እና ህዝብ ለመበታተን ዓላማዎች መጠቀም በግልፅ የተከለከለ ነው። (WA Criminal Justice Training Commission Canine Model Policy (የዋሺንግተን የወንጀል ፍትህ ማሰልጠኛ ኮሚሽን የውሻ ሞዴል ፖሊሲ)።)

(4) የሕክምና እርዳታ

በህግ አስከባሪዎች ቁጥጥር ስር ባለው ቦታ ላይ፣ ባለው የመጀመሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ እድል፣ ኦፊሰሮች ጉዳት ለደረሰባቸው፣ በኃይል አጠቃቀም ህመም እንደደረሰባቸው ቅሬታ ላቀረቡ ወይም ለኬሚካል ነገሮች ከተጋለጡ በኋላ እርዳታ ለሚፈልጉ ሰዎች የመጀመሪያ እርዳታ መስጠት ወይም ማመቻቸት አለባቸው። (RCW 36.28A.445)።

(5) ሪፖርት ማድረግ

በሕዝብ ቁጥጥር ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ሁሉም የአካላዊ ኃይል አጠቃቀሞች ሪፖርት፣ ምርመራ እና ግምገማ ላይ በወጣው ፖሊሲ መሰረት ሪፖርት ሊደረጉ፣ ሊመረመሩ እና ሊገመገሙ ይገባል። የእንደዚህ አይነት ክስተቶች መጠን ከፍ ማለት እና የአካላዊ ኃይል ተገዢዎች በቁጥጥር ስር የመቆየት እድላቸው ከፍ ማለት፣ በተለመደው የኃይል ግምገማ ፕሮቶኮሎች ለማሰራጨት እንደ ምክንያት አይቆጠርም።